# የመጀመሪያውን አምስት ዓመት ዕቅድ እያሳካ ያለ ተቋም

ሰለሞን ገበየሁ 12-15-14

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተወጠነው የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ አብዛኛው በተያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ እየተካሄደ ነው። አመርቂ ውጤት እየተገኘበት መሆኑም ይታወቃል። ዕቅዱ የሀገሪቱን ግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር የልማት ስትራቴጂ ማሸጋገር ይቻል ዘንድ በቂ መደላድል ይፈጥራል፡፡

ታዲያ ሃቁን በማያሻማ ሁኔታ የተረዱት መንግስትና የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የመጀመሪያውን የአምስት ዓመት ዕቅድ በውጤታማነት ለመደምደም በሁሉም መስኮች ከፍተኛ ርብርብ እያደረጉ ነው፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው በዕቅዱ ውስጥ የሚገኙት የልማት ዘርፎች በርካታ ናቸው። ከእነዚህ መካከል አንዱና ዋነኛው የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ነው። እናም በዚህ ፅሑፌ ይህ ግዙፍ ኮርፖሬሽን በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተቀመጠለትን ዕቅድ ከማሳካት አኳያ ባለፉት ሶስት ዓመታት ያከናወናቸውን ሰፋፊ የልማት ስራዎችን ለውድ አንባቢዎቼ በመጠኑ ለማስቃኘት እንሞክራለሁ። በቅድሚያ ግን ተቋሙ የተቋቋመበት ዓላማና ግቦች ምን እንደሚመስሉ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የኢንዱስትሪው ዘርፍ ቀልጣፋ ሚና እንዲጫወት ለማስቻል ከተቋቋሙት የልማት ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ተቋም ነው።

መንግስት ባስመቀጠው አቅጣጫ እየታገዘ ሀገሪቱ ያላትን የቴክኖሎጂ አቅም በማቀናጀትና በማስተባባር ወደ ኢንዱስትሪያይዜሽን የሚደረገውን ሽግግር ለማቀላጠፍ ብሎም ኢንዱስትሪው የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለመምራት የሚያስችለውን ሁኔታ ለማመቻቸት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 183/2002 በአስር ቢሊዮን ብር የተቋቋመ መንግስታዊ ድርጅትም ነው፡፡

ይህ ታላቅ የልማት ተቋም ሲቋቋም የሀገራችን ግብርና መር ስትራቴጂ ወደ ኢንዱስትሪ መር እንዲሸጋገር መደላድል የመፍጠር ዓላማ አንግቦ ሲሆን፤ ዓላማውን ማሳካት ይቻለው ዘንድ የተነጠሩ ግቦችን ይዟል፡፡

ተቋሙ ይዟቸው ከተነሳው ግቦች መካከል ሀገሪቱ ከውጭ የምታስመጣቸው ብረታ ብረት ፣ ማሽነሪዎችና መለዋወጫዎች ሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪ እጥረትን በከፍተኛ መጠን መቅረፍ ነው። በዚህም የማምረቻ ፋብሪካዎችን በሀገር ውስጥ በማምረትና አቅማቸውን በማሳደግ ከፍተኛና ፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማረጋገጥ መጠነ ሰፊ የኢንቨስትመንት ዕድል በማመቻቸት የስራ ዕድል መፍጠር ችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን ለመደገፍና ለማስተሳሰር እንዲሁም የአነስተኛ ጥቃቅን ተቋሞችን ከማኒፋክቸሪንግ የልማት ሆነ የአገልግሎት ዘርፍ ተቋማት ጋር በማስተሳሰር እንዲጠናከሩ ማስቻል ብሎም የአሰራርና የቴክኖሎጂ አቅማቸውን በመገንባት ወደ ቀጣዩ የዕድገት እርከን የሚያሸጋግራቸውን ድጋፍና ትብብር ለማከናወን እንዲሁም ትላልቅ የመንግስት የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን መስራትና መገንባትን የመሳሰሉ ግቦችን ያነገበ ተቋም ነው፡፡

ተቋሙ ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውን ዓላማና ግቦችን ተመርኩዞ ሲቋቋም በስሩ በርካታ ኢንዱስትሪዎችን አቅፎ ወደ ትግበራ መግባቱ ይታወሳል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በስሩ የሚገኙት የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ቁጥራቸው አስራ ሰባት ደርሷል፡፡

ይህ ታላቅ መንግስታዊ የልማት ተቋም በሀገራችን ፈር ቀዳጅ የልማት ሞተር በመሆን የህዳሴ ጉዟችንን ለማረጋገጥ እየተደረገ ባለው ሰፊ ጥረት ተልዕኮውን በሚገባ እየተወጣ ነው፡፡

መንግስት የነደፈውን በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ የሀገር ውስጥ ምርት በዋጋ መጠን 104.1 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ያለመ ነው፡፡ የነፍስ ወከፍ ብረት ፍጆታ ደግሞ 34 ነጥብ 72 ኪሎ ግራም ማድረስ ነው።

የአቅም አጠቃቀሙንም በልማት ዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 95 በመቶ ከፍ እንዲል በማድረግ፣ ለዋና ዋና የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችንና አካላትን በሀገር ውስጥ በማምረት ኢንቬስተሮችን የመደገፍ አቅም መፍጠር የሚሉ ተግባራትም ከዋና ዋና ግቦች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ሀገራችን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር መደላድል በመፍጠር እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግለው የአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በዕቅዱ ሂደትም የኢንዱስትሪው ዘርፍ የተረካቢነት ሚናው እንዲረጋገጥ በየዘርፉ በግልጽ የተቀመጡ ዕቅዶችን ማስፈጸም የግድ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

በዚህም መሰረት የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገትን በመሰረታዊው አማራጭ 11 በመቶ፣ በከፍተኛው የዕድገት አማራጭ 14 ነጥብ 9 በመቶ ለማሳደግ ከተጣለው ግብ ውስጥ ኢንዱስትሪው በየዓመቱ እስከ 20 በመቶ ዕድገት ያስመዘግባል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ይህ ሁኔታ እስከ አሁን ካለው ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር በጥሩ መንገድ እየሄደ መሆኑን እየተመዘገቡ የሚገኙ የምጣኔ ሐብት ዕድገቶች ያመላክቱናል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በ2005 ዓ.ም መጨረሻ በ18 ነጥብ 5 በመቶ ዕድገት ማሳየቱ ነው። ይህም ከሚፈለገው የእመርታ መጠን ጋር በእጅጉ የተቀራረበ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በ2006ትም ከዚህ በላይ መመዝገቡ እንዲሁ።

ከዚህ አኳያ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ላይ ከሚያከናውናቸው ታላላቅ ተግባሮች መካከል በኃይል ማመንጫ፣ ማሰራጫና መሳሪያዎች የመፈብረክ ኃላፊነቱን በብቃት በመወጣት ላይ ይገኛል። እናም በዕቅድ ዘመኑ የሶስት ዓመት አፈጻጸሙ ሲታይ አመርቂ ነበር፡፡

ተቋሙ የተሰጠው የስራ ድርሻ ሁሉንም የሃይል ማመንጫ አውታሮችን የሚመለከት ቢሆንም፣ በተለይም በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የግንባታውን ሃምሳ በመቶ የስራ ተቋራጭ ኃላፊነት ወስዶ በመስራት ላይ ነው፡፡ በእስከ አሁኑ እንቅስቃሴውም ወገንን የሚያኮራና ሀገርን የሚጠቅም ፍጻሜዎችን ከውኗል፡፡

በአራት ዓመት የአፈጻጸም ሂደቱ ላይ በእጅጉ ለውጤት ካበቃባቸው ተግባራት መካከል በሃድሮ መካኒካልና በሃይድሮሊክ ስቲልስትራክቸር ያከናወነው የዲዛይን ማስተካከያና ማሻሻያ ስራ፤ ታቅዶ የነበረውን የግድቡ የኃይል ማመንጨት አቅምን በ750 ሜጋዋት በማሳደግ ከ5250 ሜጋ ዋት ወደ ወደ ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት ከፍ እንዲል ማድረጉ ነው፡፡

ተቋሙ ይህን የሚያኮራ ታላቅ ስራ ያከናውነው የህዳሴ ግድቡ ግንባታ ዕውን ከሆነ ከአንድ ዓመት በኋላ እንደበር ሁላችንም የምናስታውሰው ሃቅ ነው፡፡ በዚህ የዲዛይን ማሻሻያ ስራም ለህዳሴ ግድቡ ከተያዘው በጀት አራት ቢሊዮን ብር የሚያህል ወጪን ለማዳን ችሏል፡፡

በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከንፋስና ከፀሐይ ሃይሎች እንዲሁም ከእንፋሎትና ከሌሎች አማራጭ ፀጋዎች ተጨማሪ የሃይል አቅርቦትን ለማምረት ያልተቋረጠ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የኤሌትሪክ ሃይል ማሰራጫ ትራንስፎርመሮች የማምረትና የማደስ አገልግሎት በሚሰጥ ማዕከሉ አማካኝነት በቀን ሃያ ትራንስፎርመሮች በማምረት ላይም ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እስከ አሁን ለተገነቡትና ወደፊት ለሚገነቡት የሃይል ማመንጫ አውታሮች ሃይልን ለማሰራጨት የሚያገለግሉ ኬብሎችንና ሽቦዎችን በተለያየ ዓይነትና መጠን የሚችል ግዙፍ ፋብሪካ ገንብቷል።

የተከላና የዝርጋታ ስልቶችም ተጠናቅቀው አሁን በተጨባጭ በስራ ላይ እየዋለ ያለውን አንድ ሺ ሁለት መቶ ቶን የሚመዘን ብረት አምርቶ ተከላው እየተከናወነ ይገኛል፡፡ የህዳሴው ግድብ ሶስተኛ ዓመቱ እየተከበረ ባለበት በአሁኑ ወቅት የብረት ተከላና የአርማታ ሙሌቱ በእጅጉ እየተፋጠነ ነው፡፡

የኤሌክትሮ መካኒካል መስሪያዎችን በሚመለከትም ለቅድመ ሃይል ማመንጨት ፕሮግራም የሚያስፈልጉ ሁለት ተርባይኖችንና ጄኔሬተሮችን ከአጋር አምራች ድርጅቶች ጋር በመሆን እየሰራ ነው።

እንደሚታወቀው የመንግስት ቀዳሚውና ዋነኛ የልማት የዕድገት ስትራቴጂ ግብርናንና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የግብርና ምርትን በእጥፍ የማሳደግ አቅጣጫ ተቀይሶ ለግቡ ስኬት መንግስትና ህዝብ መረባረብ ላይ ናቸው፡፡

መንግስት፣ ታታሪው አርሶ አደርና መላው ህዝብ እጅና ጓንት በመሆን እያከናወኑ ያሉትን ሰፊ እንቅስቃሴ ተጨባጭ ውጤት እያስገኙበት እንደሆነ ዓለም እየመሰከረ ነው፡፡ በዚህ ረገድም በግርብርናው ዘርፍ የኢኮኖሚውን ዘርፍ ለማንቀሳቀስ ከፍተኛ ኮርፖሬሽኑ የበኩሉን ሚና እየተጫወተ ነው።

አዎ! በዚህ ዘርፍ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ወገቡን ጠበቅ አድርጎ እየሰራ ነው፡፡ እናም እዚህ ላይ ባለፉት ሶስት ዓመታት ያከናወናቸውን ተግባራት የተወሰኑትን መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡

ኮርፖሬሽኑ ለአነስተኛ የአርሶ አደር ማሳዎች የእርሻ ስራ የሚያገለግሉ የተለያዩ ሞዴልና የፈረስ ጉልበት ያላቸው አምሰት ሺህ አንድ መቶ አምስት ትራክተሮችን ከነ ሙሉ አባሪዎቻቸው አሟልቶ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና አራት የእርሻ መሣሪያዎች አምርቶ ለአርሶ አደሩ ያቀረበ ሲሆን፤ በዚህም አርሶ አደሩ ምርቱን በአጥፍ እያዲያሳድግ ከፍተኛ ዕገዛ ማበርከት ችሏል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም የተለያየ ይዘት ያላቸው ሰንተርፊጋል ፖምፖችና ከነ መለዋወጫቸው በማምረት ላይ ይገኛል፡፡

መንግስት በአምስት ዓመቱ የልማት ዕቅድ የግብርና ዘርፍ በእጥፍ ለማሳደግ የሚያስችሉና ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው ማዳበሪያ መሆኑን በግልፅ አስቀምጧል። ይህን ትልም ዕውን ለማድረግም ኮርፖሬሽኑ እያንዳዳቸው ሶስት መቶ ሺህ ቶን የማምረት አቅም ያላቸውን አስር የማዳበሪያ ማምረቻ ፋብሪካዎች በመገንባት ላይ ነው፡፡

ከዚህ ባሻገርም የሀገራችንን ኢኮኖሚን በከፍተኛ ደረጃ እየተቀራመተ ያለውን የነዳጅ ፍጆታ ሊተኩ የሚችሉ የባዮፊውል፣ የባዮማስና ሲንተቲክ ናፍጣ ምርቶችን ለማምረት

የጥናት፣ የምርምርና የሙከራ ተግባራትን እየከወነ ይገኛል፡፡ ለዚህ ተግባር የሚያገለገሉ ተክሎችን ለይቶ በተለያዩ አካባቢዎች ምርት ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ስፋፊ የእርሻ ቦታዎችን አዘጋጅቶ ወደ ስራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ነው፡፡

ምንም እንኳን ከዕቅድ አኳያ ሙሉ በሙሉ ወደ ትግበራ ተገብቷል ባይባልም፤ በአንዳንድ አካባቢዎች በቴክኖሎጂ እየታገዘ የጀትሮፍ ተክልን በስፋት በማምረት ነዳጅን የመተካት ስራን በተገቢው መንገድ እየተወጣ ነው ማለት ይቻላል፡፡

'ሀገራችን እንደ ወትሮው ቴክኖሎጂ የምትሸምት ወይም የምትዋስ ሀገር መሆኗ ማብቃት አለበት' የሚል ጽኑ እምነት ያለው ተቋሙ፤ ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን በአመርቂ ደረጃ በመቅሰም ሀገራችን የራሷ ቴክኖሊጂ ያላት እንድትሆን ለማድረግ መጠነ ሰፊ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ተቋሙ የሀገራችን ቴክኖሎጂ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ተገንዝቦ ስራ ላይ ያለውንና ዕምቅ ሀብቷን በማጤን በመስኩ የሚገኘውን ተጨባጭ የሰው ሃይልን ዕውቀትና አቅም በማቀናጀት ወደሚፈለገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረስ ልዩ ትኩረትና አቅጣጫን ቀይሶ በትጋት እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በመከናወን ላይ የሚገኙ በርካታ የልማት ዕድገቶች በራሳችን ዜጎች የሚከናወኑበት ሁኔታ መፍጠር አለበት የሚለውን የመንግስት አቋም በመያዝ ተግባራዊ ስራዎችን እያሳለጠ ነው፡፡ በመሆኑም በአብዛኛዎቹ ኢንዱስትሪዎች የጥናትና ምርምር ማዕከላት በማቋቋም ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

እነዚህ የተቋሙ የምርምርና የፈጠራ ውጤቶች እጅግ ተስፋ ሰጪ ናቸው። እርግጥም "ይቻላል" በሚል መንፈስ ከተነሱ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል በተግባር በማሳየት ላይ የሚገኘው ይህ ተቋም፤ በሀገሪቱ ውስጥ የሚዘረጉ የልማት አውታሮችን በራስ አቅም ለመገንባት መንግስት የያዘውን አቅጣጫ እያንፀባረቀ ነው። በህብረተሰቡ ዘንድ ልማታዊ አስተሳሰቦች እንዲሰርፁ የበኩሉን ሚና እየተጫወተ መሆኑም እንዲሁ፡፡ እርግጥ ቴክኖሎጂ ከአስተሳሰብ የሚመነጭ በመሆኑ፤ የአስተሳሰብ ለውጥ ከመጣ የቴክኖሎጂ ሽግግሩ ስለሚፋጠን የተቋሙ ስራ ይበል የሚያሰ" ነው፡፡

እንደ ዕውነቱ ከሆነ በልማት ዕቅዱ አራት ዓመታት ተቋሙ የሚያመርታቸው ምርቶችና የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በኢትዮጵያ የሚታሰቡ አልነበሩም ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡

ይሁንና እነዚህን ተግባራት ለማከናወን ተቋሙ ደፍሮ መግባቱ ለቴክኖሎጂ ሽግግር ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህም ለአብነት ያህል አሁን በተጨባጭ በኮርፖሬሽኑ እየተመረቱ ካሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች መካከል፤ ሞተሮችን፣ ጄኔሬተሮችን፣ ሶላር ፕኔሎችንና ኮምፓክት ሰብስቴሽኖችን የማምረትና የማደስ ስራ እንዲሁም ሽቦዎችንና ኬብሎችን የመፈብረክ ተግባራቶችን በጥቂቱ መጥቀስ ተቋሙ ምን ያህል በቴክኖሎጂ ሽግግር ውስጥ ሆኖ እየሰራ መሆኑን የሚያመላክቱ ዕውነታዎች ናቸው፡፡

እንደሚታወቀው ልማትን ለማፋጠን የትራንስፖርት አጋዥነት ወሳኝ ስለሆነ፤ የትራንስፖርት ኢንዱስትሪው የግድ እየዘመነና እየተስፋፋ መሄድ አለበት፡፡ ከዚህ አኳያም ተቋሙ የሀገራችን ከተሞች እያጋጠማቸው የሚገኘውን ከፍተኛ የትራንስፖርት ችግር ለመፍታት የከተማ አውቶቡሶችን፣ ሚኒባሶችንና ሚድባሶችን በማምረት አዲስ አበባን ጨምሮ ለተለያዩ የክልል ከተሞች አቅርቧል፤ በማምረት ላይም ይገኛል።

መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች፣ ለልማትና የኢንቨስትመንት ተቋማት እንዲሁም ለባለ ሃብቶች የሚያገለግሉ ፒክአፖችን (ደብልና ሲንግል ካብ)፣ ስቴሽን ዋገኖችን ብሎም ሞተር ብስክሌቶችንም በጥራትና በብዛት እያመረተ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የጭነት ትራኮች፣ ቦቲዎችና ዲሞትራኮችን እያመረተ የጭነት የትራንስፖርት ችግሩን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቃቀለል የማድረግ ኃላፊነቱን እየተወጣ ነው፡፡

በጥቅሉ ባለፉት አራት ዓመታት ብቻ ተቋሙ ከ500 መቶ በላይ የከተማ አብቶብሶችን በመገጣጠም ለአዲስ አበባና ለክልል ከተሞች በማስረከብ የሀገሪቱ የትራንስፖርት እጥረት እንዲቃለል የበኩሉን ጥረት አድርጓል፡፡ ስድስት ሺህ ያህል ቀላልና ከባድ

የኮንስትራክሽን ማሽኖችንና አንድ መቶ ዘጠኝ የጭነት ተሽከርካሪዎችን ገጣጥሞ በስራ ላይ እንዲውሉ ማድረጉም ካከናወናቸው ታላላቅ ስራዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ይህ ብቻ አይደለም። መንግስት በዘላቂነት የሀገሪቱን የትራንስፖርት ችግር ለማቃለል እያከናወነ ባለው ስራ፤ ከአዲስ አበባ ቀላል ባቡር እስከ ትላልቆቹ ሀገር አቋራጭ ባቡሮች ፋስሊቲዎችን ከመገንባት ባሻገር፣ በተለይም ቀላል የከተማ ባቡርን ሙሉ በሙሉ ማለትም ከዲዛይን ጀምሮ የመገጣጠምና የኤሌትሪክ ዝርጋታን ስራዎች እያከናወነ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የባቡር ፉርጎዎች በኮርፖሬሽኑ እየተመረቱ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የአዲስ አበባን ቀላል የባቡር ስራን ከግማሽ በላይ መጠናቀቁ መንግስት ይፋ ማድረጉ የሚታወቅ ሲሆን፤ ለዚህ ዕመርታ የተቋሙ ሃላፊነት የተሞላበት ሁለገብ ድጋፍ በእጅጉ የሚደነቅ ነው፡፡

ሀገራችን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ልማት ለምታደርገው ሽግግር የኢንዱስትሪ ማዕከላትና ሌሎች የልማቱ አጋዥ ዘርፎች መሰረታቸው የሚጣልበት ወቅት አሁን መሆኑ ከማንም የሚሰወር ጉዳይ አይመስለኝም፡፡

ታዲያ ይህን ልማታዊ ትልም ዕውን ለማድረግ የሚቻለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አቅም መገንባት ሲቻል እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ኮርፖሬሽኑ እያመረታቸው የሚገኙት አነስተኛና ከፍተኛ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ዓይነተኛ መፍትሔ መሆን እየቻሉ ነው፡፡

እነዚህ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች በሀገሪቱ ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በማስፋፋት እንዲሁም ከተሞችን፣ ንዑስ ከተሞችንና የገጠር ቀበሌዎችን በማገናኘት የህዝቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስሮች እያጠናከሩ ናቸው፡፡ ከምርቶቹ ውስጥ ሎደር፣ ፎርክሊፍት፣ ግሬደር፣ ዶዘር፣ ሮላር፣ ዳምፐር፣ ትሬለር እና ኮምፖክተር በዋነኝነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተቋሙ አመርቂ ውጤት እያስመዘገባቸው ካሉ ስራዎች መካከል አዳዲስ የስኳር ፋብሪካዎችን የመገንባት እንዲሁም በነባር የስኳር ፋብሪካዎች ውስጥ የማስፋፋት

ፕሮጀክቶችን የማከናወን ተግባራት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ አስር አዳዲስ የስኳር ፋብሪካዎች በተለያዩ ክልሎች በፍጥነት እየተገነቡ ናቸው፡፡

እነዚህ የስኳር ፋብሪካዎች ግንባታቸው ሲጠናቀቅ ሁለት መቶ ሃምሳ ቶን ስኳር ማምረት ይችላሉ፡፡ በዚህም በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ያሉ ፋብሪካዎች ከሚያመርቱት ሶስት መቶ ሺህ ቶን ገደማ የሚሆን የስኳር ምርት፤ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ ሁለት ነጥብ ሃያ አምስት ሚሊዮን ቶን እንዲደርስ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ዕቅዱ ከተሳካ ሀገራችንን ወደ ላቀ የዕድገት ምዕራፍ የሚያሸጋግር እንደሆነ በመተማመን ለተፈጻሚነቱ ከመንግስት ጎን በመቆም ያደረገውና እያደረገ ያለው ርብርብ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ጥቂት የኢትዮጵያን ዕድገትና የህዝቦቿን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ማየት የማይሹ ሃይሎች ግን ስኬታማነቱን ከወዲሁ እያስመሰከረ ያለውን የልማት ትልም ገና ከጅምሩ ‘ሊሳካ የማይችል፣ በሰማይ ላይ የተንጠለጠለ፣ ከንቱ ተስፋ…ምንትስ’ እያሉ ሲያጥላሉት እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

ሆኖም በዕቅዱ ላይ በእነዚህ ወገኖች የተሰነዘሩት የተቃውሞ ሃሳቦች መሰረተ-ቢስ መሆናቸው መንግስትና መላው ህዝብ ይህን ታላቅ የለውጥ ዕቅድ ያለምን ፈራ ተባ አቅማቸው በፈቀደ መጠን ዕውን እንደሚያደርጉት ከእስካሁኑ የሶስት ዓመት ስኬታማ አፈፃፀማቸው በመነሳት ለመናገር አይከብድም–“የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል” እንዲል የሀገራችን አርሶ አደር።

እርግጥ እንዲህ ዓይነቱ በዓይን የሚታይ ልማትን የማጣጣል አባዜ የተጠናወታቸው ጥቂት ሃይሎች ቀደም ሲል በመጠኑ የጠቀስኳቸውን ከፍተኛ ተግባራትን እያከናወነ ባለው በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ላይ ሳይቀር በወሬ ጥላሸት ሲቀቡ ተስተውለዋል። እነዚህ ወገኖች ኮርፖሬሽኑ የያዘውን ዕቅድ ሊያሳካው አይችልም ከማለት ባለፈም ተቋሙ በሁሉም ዘርፍ እየተሳተፈ በመሆኑ የግሉን ዘርፍ ሊያቀጭጨው እንደሚችል አስመስለው ከመናገር ወደ ኋላ አላሉም፡፡

ዳሩ ግን እነዚህ ሃይሎች በእውር ድንብሩ ከማውራት ውጪ ያልተገነዘቡት ጉዳይ ሀገራችን የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከመጀመሩ በፊት ለሰባት ተከታታይ ዓመታት ባለሁለት አሃዝ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እያስመዘገበች የመጣች መሆኑን ነው፡፡

እናም "የነብርን ጭራ አይዙም፣ ከያዙም አይለቁም" እንዲል የሀገራችን ሰው፤ ለዘመናት በድህነት አረንቋ ውስጥ ሲዳክር የነበረ ህዝብ አሁን መንግስት በቀየሳቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመመራት ያስመዘገበውንና እያስመዘገበ ያለውን ልማታዊ ዕድገት አጠናክሮ የሚቀጥል እንጂ ወደ ኋላ ያፈገፍጋል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡

ተቋሙም የዚሁ ህዝብና መንግስት አካል ነውና የያዘውን ዕቅድ የማያሳካበት ምንም ምክንያት የለም። እርግጥ ማንኛውም ወገን በዓይን የሚታይ ገሃድ ጉዳይ መካድ ከፈለገ፤ ድንጋይን 'ዳቦ ነው' ብሎ ሊከራከር ስለሚችል የእነዚህ ወገኖችን አሉባልታ ከመጤፍ የሚቆጥረው ሰው የሚገኝ አይመስለኝም።

ከዚህ ጎን ለጎንም ተቋሙ በሁሉም የልማት ዘርፎች መሳተፉ የግሉን ዘርፍ የሚያቀጭጨው አይደለም—በተገላቢጦሹ የግሉ ዘርፍ እንዲያድግ ያደርጋል እንጂ። እንደ እውነቱ ከሆነ የልማት ደንቃራዎቹ እንደሚወጡት አቃቂር ሳይሆን፤ ተቋሙ በአብሮ መስራትና ማደግ ላይ አትኩሮ የሚሰራ ነው።

ብቻውን ልደግ የሚል ራዕይን ያነገበም አይደለም፡፡ እንዲያውም የኮርፖሬሽኑ ዋነኛ ዓላማ ሌሎች የቴክኖሎጂ ሽግግርን የሚፈጥሩ የመንግስትና የግል ተቋማትን በመደገፍ ማሳደግ ነው፡፡

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የእነዚያ ታላላቅ ልማታዊ ተግባራት ከዋኝ የሆነው "ብኢኮ" የግሉን ዘርፍ የሚያቀጭጭ አሊያም ጎሮሮ የሚዘጋ ሳይሆን፤ ከእነዚህ የግል ዘርፎች ጋር እየተመጋገበ የሀገሪቱን የህዳሴ ጉዞ የማሳካት ራዕይን ያነገበ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም ተቋሙ ከስምንት መቶ በላይ ከሚሆኑ አጋሮች ጋር አብሮ እየሰራ መሆኑ ይህን ዕውነታ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው ጉዳይ ኮርፖሬሽኑ ራሱ ሊሰራቸው የማይገቡ ስራዎችን ሙሉ በሙሉ ለግሉ ዘርፍ እያስተላለፈ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ ስራዎቹን ከማስተላለፍ ባሻገርም የበርካታ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አቅምን የማሳደግ ታላቅ ተግባርን እየከወነ ነው፡፡

እነዚህ ክንዋኔዎቹም ተቋሙ የግሉን ዘርፍ እያጠናከረና በቀጣይም በኢንዱስትሪ መሩ ልማታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አቅማቸው ጎልብቶ ሀገራቸውን እንዲገነቡ እያደረገ እንጂ ስራ ፈቶች እንደሚያወሩት እያቀጨጫቸው አይደለም። እያፋፋቸው ነው።

እናም ተቋሙ የያዛቸውን ሰፋፊ ስራዎች ለግሉ ዘርፍ ስራን ከመስጠት ባለፈ አቅማቸውን የመገንባት ተግባራትንም ስለሚያጠቃልል የአሉባልተኞቹ ወሬ ቅመራ ይህ ነው የሚባል ትኩረት የመሰጠው አይደለም።

ለነገሩ ተቋሙ በልማት ዕቅዱ ላይ የተሰጠው ሀገራዊ ኃላፊነት መዘናጋትን የማይጠይቅ በመሆኑ፤ ባለፉት ሶስት ዓመታት ያከናወናቸውንና እያከናወናቸው ያሉትን ሰፋፊ ፕሮጀክቶች በቀሪዎቹ የዕቅዱ ዓመታት ከግብ ማድረሱ አይቀሬ ነው። ይህም በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስኬታማነት ላይ የራሱን ስኬታማ ሚና እንዲወጣ ያደርገዋል፡፡

የተቋሙና የሌሎች የልማት ዕቅዱ ተዋንያን ድምር ውጤትም የሀገራችንን ህዳሴ ለማረጋገጥ በሚደረገው ሁለገባዊ ጥረት ከብረት የጠነከረ መደላድልን መፍጠሩ አይቀሬ ነው።

"የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል" እንደሚባለው ተቋሙ ካሉበት ሌሎች ተጓዳኝ ስራዎች በተጨማሪ በተለያዩ መስኮች የሀገራችንን ህዳሴ ቅርብ ለማድረግ ከሌሎች አካላት ጋር በመሆን የሚያከናውነው ስራ ሊደነቅ ይገባል ባይ ነኝ።